# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋሚያ ድጋፍ ማዕቀፍ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 30/2013

# ማውጫ


ክፍል አንድ ..............................................................5

ጠቅላላ ድንጋጌዎች ..............................................................5

1. አጭር ርዕስ ..............................................................5
2. ትርጓሜ ..............................................................5
3. የተፈፃሚነት ወሰን ..............................................................7
4. የፆታ አገላለጽ ..............................................................7

ክፍል ሁለት ..............................................................8

ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓለማ እና መርሆዎች ..............................................................8

5. ራዕይ ..............................................................8
6. ተልዕኮ ..............................................................8
9. መርሆዎች፤ ..............................................................9

ክፍል ሶስት ..............................................................10

የደጋፍ አሰጣጥ ማዕቀፍ ..............................................................10

*10. የድጋፍ ማዕቀፍ ዓላማ ..............................................................10*
*11. የድጋፍ ተጠቃሚ አካላት ..............................................................10*

ክፍል አራት ..............................................................11

ቀድም ሲል በልማት ምክንያት ስለተነሱ አርሶ አደሮች ..............................................................11

ስለሚሰጥ ድጋፍና አተገባበር፤ ..............................................................11

16. መካከለኛ ገቢ ላላቸዉ ተጠቃሚዎች ..............................................................15
17. ከፍተኛ ገቢ ላላቸዉ ተጠቃሚዎች ..............................................................16
18. ድጋፍ ስለሚደረግበት ሁኔታ፤ ..............................................................18

ክፍል አምስት ..............................................................19

19. ወደ ፊት በልማት ምክንያት ከይዞታቸው እንዲነሱ ስለሚደረጉ አርሶ አደሮች ስለሚሰጥ ድጋፍ፣ ......19

ክፍል ስድስት ..............................................................21

የባለድርሻ አካላት ሚና ..............................................................21

20. የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋም ፕሮጀክት ተጠቃሚዎች ሚና ..............................................................21
21. የህብረተሰቡ ሚና ..............................................................21
22. የአስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ሚና ..............................................................22

*22.1. የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ ሚና፤ ..............................................................22*
*22.2. የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሚና ..............................................................22*
*22.3. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ሚና ..............................................................22*
*22.4. የንግድ ቢሮ ሚና ..............................................................23*
*22.5. የጤና ቢሮ ሚና ..............................................................24*
*22.6. የትምህርት ቢሮ ሚና ..............................................................24*
*22.7. የመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ሚና ..............................................................24*
*22.8. የኮንስትራክሽን ቢሮ ሚና ..............................................................25*

*22.9. የኢንዱስትሪ ቢሮ* .......... 25
*22.10. የአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም ሚና* .......... 25
*22.11. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ ሚና* .......... 26
*22.12. የአዲስ ካፒታል እቃ ፋይናስ ንግድ ስራ አክሲዮን ማህበር፣* .......... 26
*22.13. የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከል ሚና* .......... 27
*22.14. የውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ሚና* .......... 27
*22.15. የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን* .......... 27
*22.16. የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል እና አገልግሎት ሚና* .......... 28
*22.17. የኢፌዲሪ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ሚና* .......... 28
*22.18. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሚና* .......... 29
*22.19. የማህበራዊ ጥበቃ ፈንድ እና ልማታዊ ሴፍቲኔት ኤጀንሲ* .......... 29

ክፍል ስድስት .......... 30

ክልከላ ፣ኃላፊነት እና ቅሬታና አቤቱታ የማቅረብ መብት .......... 30

23. የተከለከሉ ድርጊቶች፣ .......... 30
24. የድጋፍ ፈላጊው ኃላፊነት .......... 31
25. የድጋፍ አመቻችና የመዝጋቢው አካል ኃላፊነት .......... 31
26. የቅሬታና አቤቱታ የማቅረብ መብት .......... 32
27. ስለ ቅሬታና አቤቱታ አቀራረብ .......... 32

ክፍል ሰባት .......... 33

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች .......... 33

28. ልዩ ልዩ ድጋፎች ስለሚደረጉበት አግባብ .......... 33
29. የመተባበር ግዴታ፣ .......... 33
*ማንኛውም ሰው ይህን መመሪያ ከማስፈጸም አኳያ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡* .......... 33
30. ቅጣት፣ .......... 33
31. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች .......... 33
*ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡* .......... 33
32. *መመሪያ የማሻሻል ስልጣን* .......... 34
*ይህን መመሪያ ማሻሻል ሲያስፈልግ ቢሮው ሊሻሻል ይችላል፡* .......... 34
33. የትርጉም አሻሚነትን በተመለከተ .......... 34
34. *መመሪያዉ የሚፀናበት ጊዜ* .......... 34

## መግቢያ

የከተማዋን እድገት ለማፋጠን ሲባል በሚደረገው የልማት እንቅስቃሴ ምክንያት በልማት ማስፋፊያ አካባቢዎች ውስጥ የሚኖሩ አርሶ አድሮች ከይዞታቸው እንዲነሱ እየተደረገ የቆየ በመሆኑ እና ወደፊትም ከይዞታቸው የሚነሱ ስለሆነ ከይዞታቸው የተነሱና የሚነሱ ዜጎች ላይ የሚፈጠረውን መፈናቀልና ልዩ ልዩ ችግሮችን በቅድሚያ ለመከላከልና ለኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግር ተጋላጭ በመሆን የደረሰባቸውንና የሚደርስባቸውን የመልካም አስተዳደር ችግር በመቅረፍ በዘላቂነት ማቋቋም በማስፈለጉ፡፡

የአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በተሻሻላው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 በተሰጠው የህግ ስልጣን መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ጽ/ቤትን በደንብ ቁጥር 79/2008 ዓ.ም እንዲቋቋም ተደረጓል፡፡

ይህ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ከተቋቋመ በኋላ በደንቡ ላይ የተገለጸውን ዓለማ እና የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር መነሻ በማድረግ በመዋቅራዊ አደረጃጀቱ መሰረት የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ተጠቃሚ መሆን ያለባቸውን በልማት ምክንያት ከይዞታቸው የተነሱትን መልሶ ማቋቋም እና በቀጣይም የሚነሱ አርሶ አደሮችን ከኢኮኖሚና ማህበራዊ ችግር ለመከላከል እና የኑሮ ሁኔታቸው እንዲሻሻል ለማድረግ በቅድሚያ የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎችን ከኪራይ ሰብሳቢነት፤ ከመልካም አስተዳር ችግሮች እንዳይጋለጡ እንዲሁም ፍህታዊነት ፤ ግልጽነትና ተጠያቂነት ባሰፈነ መልኩ በድጋፍ መስፈርቶች፣ በድጋፍ አፈጻጸም ሂደቶች እና የድጋፍ ስርዓቶች አስመልክቶ ግልጽ በሆነ መመሪያና አሰራር መፈጸም ስላለበቸዉ ይህን የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋሚያ የድጋፍ ማዕቀፍ አፈጻጸም መመሪያ ማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡

በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በልማት ተነሺ አርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 79/ 2008 ዓ.ም መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ
# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋሚያ ድጋፍ ማዕቀፍ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 30/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

2.1. **"አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡

2.2. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

2.3. **"ቢሮ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ነው፤

2.4. **"ቻርተር"** ማለት የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 ነው፤

2.5. **"ቦርድ"** ማለት የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱን ሥራ በበላይነት ለመምራት በደንብ ቁጥር 79/2008 መሰረት የተቋቋመ አካል ነው፤

2.6. **"ጽህፈት ቤት"** ማለት በደንብ ቁጥር 79/2008 መሰረት የተቋቋመ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ነው፤

2.7. **"ደንብ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ለማቋቋም በአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ የወጣው ደንብ ቁጥር 79/2008 ዓ.ም ነው፡፡

2.8. **“ሥራ አስኪያጅ”** ማለት ጽህፈት ቤቱን ለመምራት በሚመለከተው አካል የተሰየመ የበላይ ኃላፊ ነው፤

2.9. **“በልማት ተነሺ አርሶ አደር”** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ ክልል ውስጥ በግብርና ስራ ተግባር ላይ ኑሮውን መሠረት አድርጎ እየኖረ የነበረ እና እየኖረ ያለ ለልማት ሥራዎች ሲባል ከይዞታው የተነሳና የመሬት ይዞታውን ለልማት የለቀቀ አባወራ ወይም እማወራ አርሶ አደር ሲሆን ቤተሰቦቹን የሚያጠቃልል ነው፤

2.10. **“የአርሶ አደር ቤተሰብ ”** ማለት በአርሶ አደሩ ስር እየተዳደረ ያለውን የአርሶ አደሩን ልጅ፣ ሚስት ወይም ባል ነው፡፡

2.11. **“ልየታ”** ማለት በከተማው የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በተዘጋጁ ፕሮጀክቶች እና የስራ ዕድሎች በመጠቀም መልሶ በማቋቋም ተጠቃሚ የሚሆኑ አርሶ አደርና የአርሶ አደር ቤተሰቦችን የመምረጥና የማደራጀት ሂደት ነው፤

2.12. **“ተጠቃሚ“** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል በልማት ምክንያት ከይዞታቸው ተነስተው ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ችግር የተጋለጡ እና በቀጣይ በልማት ምክንያት ተነሺ ለሚሆኑ አርሶ አደሮች እና የአርሶ አደር ቤተሰቦች ናቸው፡፡

2.13. **“ምንም ገቢ የሌላቸውና መስራት የማይችሉ”** ማለት ምንም ገቢ የሌላቸውና መስራት የማይችሉ ሆነው በዕድሜ ፣ በአካል ጉዳት እና በጤና ዕክል ምክንያት ድጋፍ የሚደረግላቸው ናቸው፡፡

2.14. **“ምንም ገቢ የሌላቸውና መስራት የሚችሉ”** ማለት ምንም ገቢ የሌላቸው ሆነው ነገር ግን የስራ እድል ቢፈጠርላቸው ወይም ቢመቻችላቸው ሰርተው ኑሮዋቸውን ሊያሻሽሉ የሚችሉ ማለት ነው፡፡

2.15. **“ህጋዊ ማስረጃ”** ማለት ነዋሪነትን፣ ባለይዞታ መሆኑን የሚያስረዳ ሰነድ፣ የተከፈለ ካሳ፣ የተሰጠ ምትክ ቦታ ማስረጃ እንዲሁም ቀደም ሲል ባለይዞታና አርሶ አደር መሆኑን የሚያስረዱ ህጋዊ ሰነዶችን ከቀበሌ ወይም ወረዳ ወይም

ከክፍለ ከተማ አስተዳድር ወይም ከመሬት ልማት ማኔጅመንት ወይም በሚመለከተው አካል ተቋማት ተረጋግጦ የሚሰጥ ህጋዊ ማስረጃ ነው፡፡

2.16. **"የምዝገባና ልየታ ኮሚቴ"** ማለት ከተለያዩ አካላት ማለትም ከፕሮጀክት ጽ/ቤት፣ ከልማት ተነሺ አርሶ፣ ከወረዳ አስተዳደር እና ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት የሚወከሉ አባላት ያሉት ሆኖ በመልሶ ማቋቋም ፕሮጀክት ተጠቃሚ አርሶ አደሮችን ልየታ የሚያከናውን አደረጃት ነው፡፡

2.17. **"ባለድርሻ አካላት"** ማለት ከስራው ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያላቸው እና ተጽዕኖ ሊፈጥሩ የሚችሉ የመንግስት አካላት፣ የልማት አጋሮች፣ ተጠቃሚዎች እና የህብረተሰብ ክፍሎችን ያካተተ ነው፤

2.18. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ ነዋሪ በሆኑና በልማት ምክንያት ከይዞታቸው በተነሱና በሚነሱ አርሶ አደሮች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## 4. የፆታ አገላለጽ

የቃሉ አገባብ ሌላ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው አገላለጽ የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

# ክፍል ሁለት
# ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማ እና መርሆዎች

## 5. ራዕይ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወሰን ክልል ውስጥ የሚገኙ የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች እና ቤተሰቦቻቸው በ2013 ዓ.ም በከተማው የህዳሴ ጉዞ ፍትሃዊ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸው የተረጋገጠ ሆኖ ማየት፣

## 6. ተልዕኮ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች እና ቤተሰቦቻቸው ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞቻቸው ተጠብቆ በተቀናጀና በተደራጀ መረጃ ላይ ተመስርቶ በበቂ ቅድመ ዝግጅት በዘላቂነት መቋቋም የሚችልበትን መደላድል መፍጠር፡፡

## 7. እሴቶች

- ግልፅነት፤
- ተጠያቂነት፤
- ፍትሃዊነት፤
- የላቀ አገልግሎት መስጠት፤
- በዕውቀትና በእምነት መመራት እና መስራት፤
- ለለውጥ ዝግጁ መሆን፤
- ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን መቅረፍ፤
- ዘላቂ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፤

## 8. ዓላማ

8.1. በአስተዳደሩ ክልል ውስጥ ነዋሪ የሆኑ አርሶ አደሮች ከመደበኛ ይዞታቸው በልማት ምክንያት ሲነሱ አግባብነት ያላቸው የካሳ ክፍያዎችን መፈጸም እንደተጠበቀ ሆኖ ለተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች እንዳይጋለጡ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቅንጅት በመስራት በዘላቂነት እንዲቋቋሙ ማድረግ፣

8.2. በልማት ምክንያት ከይዞታቸው የሚነሱ አርሶ አደሮች ያላቸውን ልምድና ተሞክሮ በማገናዘብ በቀጣይነት የሚሰማሩበትን የሥራ ዘርፍ በመለየት፣ ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ ፣

8.3. በልማት ምክንያት ከይዞታቸው የሚነሱ አርሶ አደሮች የተከፈላቸውን ካሳ በዘላቂነት መጠቀም እንዲችሉ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ የኑሮ ሁኔታቸው እንዲሻሻል ማድረግ፣

8.4. የልማት ተነሽ አርሶ አደሮች ከይዞታቸው ከመነሳታቸው በፊት በቂ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ እንዲችሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራት፣

8.5. ቀደም ሲል በልማት ምክንያት ከይዞታቸው ተነስተው ለተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የተጋለጡ አርሶ አደሮችን ተገቢ መረጃዎችን በማሰባሰብና በማደራጀት በመልሶ ማቋቋም ኑሯቸው እንዲሻሻል ማድረግ፣

8.6. በልማት ምክንያት ከይዞታቸው የሚነሱ አርሶ አደሮች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ እሴቶቻቸውን በሚያስቀጥል መልኩ እና መሠረተ ልማት በተሟላበት አካባቢ የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

8.7. በማስፋፊያ አካባቢዎች ነዋሪ የሆኑ አርሶ አደሮች በልማት ምክንያት እንዲነሱ ሲደረግ በህጉ መሠረት ተገቢውን የካሳ ክፍያና ምትክ ቦታ ማግኘታቸውን መከታተልና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ መሥራት፡፡

## 9. መርሆዎች፤

9.1. ግልጽነት፣ ተጠያቂነት፣ ፍትሃዊና ተደራሽ የሆነ የድጋፍ ማዕቀፍ ለመተግበር የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት፤

9.2. በልማት ምክንያት ቀደም ብለዉ የተነሱ እና በቀጣይ የሚነሱ አርሶ አደሮችን ለማቋቋም፣ ለችግር ተጋላጭ እንዳይሆኑ ለመከላከል እና ቅንጅታዊ አሰራርን በመዘርጋት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነታቸዉን ለማረጋገጥ የሚያስችል የድጋፍ ማዕቀፍ ተግባራዊ ማድረግ፤

9.3. የድጋፍ አሰጣጥ አሰራር የህብረተሰቡ አሳታፊነትና ተደራሽነት እንዲኖረው ማድረግ፤

9.4. በልማት ምክንያት የተነሱ እና የሚነሱ አርሶ አደሮችና ቤተሰቦቻቸዉ ስለድጋፍ ማዕቀፍ አተገባበር ግልጽ መረጃ እንዲደርሳቸዉ የማድረግ ሂደት መከተል፣

9.5. የድጋፍ ማዕቀፍ አተገባበርና ድጋፍ አሰጣጥ አሰራር በዘመናዊ የመረጃ ስርዓት የተደራጀ በማድረግ ለትክክለኛ ተገልጋዮች ተደራሽነትን ማረጋገጥ፤ አላስፈላጊ ተጠቃሚነትን መከላከልና ተዓማኒነት እንዲኖር ማድረግ፡፡

## ክፍል ሶስት
## የደጋፍ አሰጣጥ ማዕቀፍ

### 10. የድጋፍ ማዕቀፍ ዓላማ

በልማት ምክንያት ከይዞታቸው የተነሱ እና የሚነሱ አርሶ አደሮች ካጋጠማቸው እና ከሚያጋጥማቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግር ለማውጣት በቅድሚያ ተገቢውን የሙያ፣ የክህሎትና የስነ-ልቦና ስልጠናዎች በመስጠት፣ በገቢ ተኮር ስራዎች በግል ወይም በማህበር ተደራጅተው በተቀረጸውና በሚመርጡት የፕሮጀክት የስራ ዘርፍ ላይ እንዲሰማሩ በማድረግ እንዲሁም በገንዘብ፣ በዓይነት እና በተለያዩ የድጋፍ ዓይነቶች በመደገፍ ፍትሃዊ ተጠቃሚነታቸውን በማረጋገጥ የኑሮ ሁኔታዎቻቸው እንዲሻሻሉ ማድረግ ነው፡፡

### 11. የድጋፍ ተጠቃሚ አካላት

11.1. በልማት ምክንያት ተነሺ የሆኑ አባወራ ወይም እማወራ አርሶ አደሮች እና ቤተሰቦቻቸው፡፡

11.2. በልማት ምክንያት በቀጣይ ተነሺ የሚሆኑ አባወራ ወይም እማወራ አርሶ አደሮች እና ቤተሰቦቻቸው፡፡

### 12. ስለሚሰጡ የድጋፍ ማዕቀፍ ዓይነቶች

ቀደም ሲል በልማት ተነሺ የሆኑ እና በቀጣይ ለሚነሱ አርሶ አደሮች ከመሰረታዊ የእለት ፍጆታ ፍላጎት ጀምሮ በዘላቂነት ለማቋቋም ስለሚሰጡ የድጋፍ ዓይነቶች፡-

12.1. የግብዓት አቅርቦት፤

12.2. የገንዘብ (መነሻ ካፒታል)፤

12.3. የኢንድስትሪ ኤክስቴሽን፤

12.4. የስልጠና ድጋፍ፤

12.5. የብድር አቅርቦት፤

12.6. የገበያ ትስስር፤

12.7. የመስሪያ ቦታ (ማምረቻ፣ ማሳያና የመሸጫ ቦታ)፤

12.8. የምክር አገልግሎት፣

12.9. የመረጃ አቅርቦት፣

12.10. ሌሎች ልዩ ልዩ ድጋፎች፡፡

# ክፍል አራት
# ቀድም ሲል በልማት ምክንያት ስለተነሱ አርሶ አደሮች ስለሚሰጥ ድጋፍና አተገባበር፤

## 13. ምንም ገቢ ለሌላቸውና መስራት ለማይችሉ የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች ስለሚሰጥ ድጋፍ ፤

በምዝገባ፣ የልየታ እና የመረጃ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 1 /2009 መሰረት ምንም ገቢ የሌላቸውና መሥራት ለማይችሉ ተብለዉ ለተለዩ ቀደም ሲል በልማት ምክንያት ከይዞታቸው ለተነሱ አርሶ አደሮች ስለሚሰጥ ድጋፍ፡-

### 13.1. የመሠረታዊ ፍላጎት ድጋፍ፤

ምንም ገቢ የሌላቸው ሆኖ መስራት ለማይችል ቤተሰብ እንደቤተሰቡ ብዛት በዓመት እንደሚከተለው ተሰልቶ በገንዘብ ድጋፍ ይደረጋል፤

ሀ. ለአንድ ሰው ብር 16,560.00 (አስራ ሺ.ህ አምስት መቶ ስልሳ ብር)፣

ለ. ከ 2 እስከ 4 ሰው ላለው ቤተሰብ ብር 20,700.00 (ሃያ ሺ. ሰባት መቶ ብር)፣

ሐ. ከ 5 በላይ 7 ሰው ላለው ቤተሰብ ብር 24,840.00 (ሃያ አራት ሺ. ስምንት መቶ አርባ ብር)፣

መ. ከ 7 በላይ ሰው ላለው ቤተሰብ ብር 28,980.00 (ሃያ ስምንት ሺ. ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ብር) ፡፡

### 13.2. የመጠለያ ድጋፍ፤

መጠለያ ለሌላቸዉ ተጠቃሚዎች በፕሮጅክት ጽህፈት ቤቱ በኩል ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የአስተዳደሩ አካላት ጋር ተቀናጅቶ በማስገንባት እንዲሰጣቸው ይደረጋል፡፡ መጠለያ እስኪዘጋጅ ድረስ በቤተሰብ በየወሩ ብር 3000.00 (ሶስት ሺ. ብር) የቤት ኪራይ ታስቦ እንዲከፍል ይደረጋል፣

### 13.3. የስልጠናና ምክር አገልግሎት ድጋፍ፤

በቋሚ መድረክ የምክር፣ መረጃና ግንዛቤ ማሻሻያ ድጋፍ በቅርንጫፍ ጽ/ቤት አማካኝነት ድጋፍ እንዲያገኙ ይደረጋል፤ ተገቢው ባለሙያ በማሳተፍ የስነልቦና ስልጠና ይሰጣል፡፡

### 13.4. በዘላቂነት ድጋፍ ስለሚደረግበት ሁኔታ፤

13.4.1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 13.1. የተገለጸው የድጋፍ አይነት እስከ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የትግበራ ጊዜ መጠናቀቅ አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ስራውን ካጠናቀቀ በኋላ ድጋፉ በቀጣይ በሚቋቋመው የአርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ ወጪ እየተደረገ እንዲከፍል ይደረጋል፣

13.4.2. በዘላቂነት የሚሰጠው የገንዘብ ድጋፍ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ወራት ወይም እንደአግባብነቱ በማንኛውም ጊዜ በስማቸው በሚከፈተው ሂሳብ ገቢ ይደረጋል፣

13.4.3. የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ በድጋፍ የሚሰጣቸውን ገንዘብ እንዲቆጥቡ እና በአግባቡ እንዲጠቀሙ የምክር፣ የስልጠና እና የክትትል ድጋፍ ይሰጣል፣

13.4.4. በከተማ አስተዳደሩ ስር በሚተዳደሩት የትራንስፖርት እና ጤና ተቋማት የነፃ አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

### 13.5. በሌላ አካል ድጋፍ ስለሚደረግበት ሁኔታ፤

በዚህ መመሪያ መሰረት በመንግስት የሚደረገው ድጋፍ እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ወይም ሌሎች በጎ አድራጎት ተቋማት ወይም ግለሰቦች የሚሰጡ ሌሎች ተጨማሪ ድጋፎች ካሉ ተጠቃሚነታቸውን ሊከለክል አይችልም፡፡

## 14. ምንም ገቢ የሌላቸውና መስራት ለሚችሉ የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች ስለሚሰጥ ድጋፍ፤

ቀደም ሲል በልማት ምክንያት ከይዞታቸው ተነስተው ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ከተጋለጡት መካከል በምዝገባ፣ የልየታ እና የመረጃ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 1/2009 መሰረት ምንም ገቢ የሌላቸዉና መስራት የሚችሉ ተብለዉ ለተለዩ ተጠቃሚዎች ስለሚሰጥ ድጋፍ፡-

## 14.1. ሰርተዉ ገቢ ማግኘት እስኪችሉ ድረስ ስለሚሰጥ ድጋፍ

በመልሶ መቋቋም ፕሮጀክት በገቢ ማስገኛ የስራ ዘርፎች እስኪሰማሩ እና ገቢ ማግኘት እስኪችሉ ድረስ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 13.1 እስከ 13.4 የተጠቀሱት የድጋፍ ዓይነቶችን ለአንድ ዓመት እንዲሰጣቸው ይደረጋል፡፡

## 14.2. በዘላቂነት ስለማቋቋም፤

14.2.1. በመረጠው የስራ መስክ በቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋም የክህሎት ስልጠና እንዲያገኝ ይደረጋል፣

14.2.2. የስልጠናው ጊዜ እስኪጠናቀቅ ድረስ በየቀኑ የትራንስፖርት እና የምሳ አበል ብር 150.00 (አንድ መቶ ሃምሳ) እንዲከፈል ይደረጋል፣

14.2.3. በከተማው አስተዳደሩ ከመንግስት ስራ ውጭ በሚገኙ የስራ እድል አማራጮች አቅምና ችሎታ ካላቸው ተገቢውን ስልጠና እንዲያገኙ በማድረግ ቅድሚያ እንዲያገኙ ይደረጋል፣

14.2.4. በመረጡት ሥራ ዘርፍ መሰረት መሰማራት ለሚፈልጉ የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች በማህበር ተደራጅተው ወደ ስራ ለመግባት የሚያስችል ስራ ማስኬጃ ወጪ ለእያንዳዱ ማህበር ፕሮጅክት ጽህፍት ቤቱ አጥንቶ በሚቀርበው ቢዝነስ ፕላን መሰረት ድጋፍ እንዲያገኙ ይደረጋል ፡፡ የገንዘቡ መጠን በቅድሚያ በቦርዱ ወይም በቢሮው እንዲፀድቅ የሚደረግ ሆኖ የስራ ማስኪጃው ከአጠቃላይ የፕሮጀክት ወጪው 10 በመቶ መብለጥ የለበትም፣

14.2.5. በማህበር ለሚደራጁ ተቋቋሚዎች የሚሆን የመስሪያ ቦታ ከስራ ዘርፋቸው ጋር የሚጣጣም ግንባታ በፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ በኩል እና በሌሎች የአስተዳደሩ አካላት ተገንብቶ እንዲሰጣቸው ይደረጋል፣

14.2.6. በማህበር ለተደራጁ እና በመረጡት የስራ ዘርፍ ለመሰማራት የሚያስችል ግብዓት በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ እንዲቀርብ የሚደረግ ሆኖ የሚቀርበው የማምረቻ መሳሪያና የቁሳቁስ ድጋፍ የዋጋውን 75% (ሀምሳ በመቶ) በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚሸፈን ሲሆን ቀሪው 25 በመቶ በተዘዋዋሪ ብድር

እስከ አራት ዓመት ተጠቃሚው እንደከፍል ይደረጋል፡፡ የብድር አመላለሱ ለአንድ ዓመት የሚቆይ የችሮታ ጊዜ እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

14.2.7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 14.2.4. እና 14.2.6 የፕሮጀክቱ አጠቃላይ ወጪ ለአንድ ማህበር እስከ 2,000,000.00 (ሁለት ሚሊዮን ብር) ድረስ ይሆናል፡፡

14.2.8. ሌሎች ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በሚሰጠው ልዩ ልዩ ድጋፎች አቅም በፈቀደ መሰረት ድጋፍና ክትትል እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

## 15. ዝቅተኛ ገቢ ያላቸዉ፣

በምዝገባ፣ የልየታ እና የመረጃ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 1 /2009 መሰረት ዝቅተኛ ገቢ ያላቸዉ ተብለዉ ለተለዩ ተጠቃሚዎች ስለሚሰጥ ድጋፎች፡-

### 15.1. በዘላቂነት ስለማቋቋም፤

15.1.1. በመረጠው የስራ መስክ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋም የክህሎት ስልጠና እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

15.1.2. የስልጠናው ጊዜ እስኪጠናቀቅ ድረስ በየቀኑ የትራንስፖርት እና የምሳ አበል ብር 150.00 (አንድ መቶ ሃምሳ) እንዲከፈል ይደረጋል፣

15.1.3. በከተማው አስተዳደሩ ከመንግስት ስራ ውጭ በሚገኙ የስራ እድል አማራጮች አቅምና ችሎታ ካላቸው ተገቢውን ስልጠና እንዲያገኙ በማድረግ ቅድሚያ እንዲያገኙ ይደረጋል፣

15.1.4. በመረጡት ሥራ ዘርፍ መሰረት መሰማራት ለሚፈልጉ የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች በማህበር ተደራጅተው ወደ ስራ ለመግባት የሚያስችል ስራ ማስኬጃ ወጪ ለእያንዳዱ ማህበር ፕሮጅክት ጽህፍት ቤቱ አጥንቶ በሚቀርበው ቢዝነስ ፕላን መሰረት ድጋፍ እንዲያገኙ ይደረጋል ፡፡ የገንዘቡ መጠን በቅድሚያ በቦርዱ ወይም በቢሮው እንዲፀድቅ የሚደረግ ሆኖ የስራ ማስኪጃው ከአጠቃላይ የፕሮጀክት ወጪው 10 በመቶ መብልጥ የለበትም፣

15.1.5. በማህበር ለሚደራጁ ተቋቋሚዎች የሚሆን የመስሪያ ቦታ ከስራ ዘርፋቸው ጋር የሚጣጣም ግንባታ በፕሮጅት ጽህፈት ቤቱ በኩል እና በሌሎች የአስተዳደሩ አካላት ተገንብቶ እንዲሰጣቸው ይደረጋል፣

15.1.6. በማህበር ለተደራጁ እና በመረጡት የስራ ዘርፍ ለመሰማራት የሚያስችል ግብዓት በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ እንዲቀርብ የሚደረግ ሆኖ የሚቀርበው የማምረቻ መሳሪያና የቁሳቁስ ድጋፍ የዋጋውን 50% (ሀምሳ በመቶ) በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚሸፈን ሲሆን ቀሪው 50 % (ሀምሳ በመቶ) በተዘዋዋሪ ብድር እስከ አራት ዓመት ተጠቃሚው እንደከፍል ይደረጋል፡፡ የብድር አመላለሱ ለአንድ ዓመት የሚቆይ የችሮታ ጊዜ እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

15.1.7. በዝቅተኛ ገቢ ኑሮ ላይ ሆነው መጠለያ የለሌላቸዉ መሆኑ ሲረጋገጥ በፕሮጅክት ጽህፈት ቤቱ በኩል ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የአስተዳደሩ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መኖሪያ ቤት በማስገንባት እንዲሰጣቸው ይደረጋል፡፡

15.1.8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 14.2.4. እና 14.2.6 የፕሮጀክቱ አጠቃላይ ወጪ ለአንድ ማህበር እስከ 2,000,000.00 (ሁለት ሚሊዮን ብር) ድረስ ይሆናል፡፡

15.1.9. ሌሎች ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በሚሰጠው ልዩ ልዩ ድጋፎች አቅም በፈቀደ መሰረት ድጋፍና ክትትል እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

## 16. መካከለኛ ገቢ ላላቸዉ ተጠቃሚዎች

በምዝገባ፣ የልየታ እና የመረጃ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 001 /2009 መሰረት መካከለኛ ገቢ ያላቸዉ ተብለዉ ለተለዩ ተጠቃሚዎች የሚሰጡ ድጋፎች፡-

### 16.1. በዘላቂነት ስለማቋቋም፤

16.1.1. በመረጠው የስራ መስክ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋም የክህሎት ስልጠና እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

16.1.2. የስልጠናው ጊዜ እስኪጠናቀቅ ድረስ በየቀኑ የትራንስፖርት እና የምሳ አበል ብር 150.00 (አንድ መቶ ሃምሳ) እንዲከፈል ይደረጋል፣

16.1.3. በመረጡት ሥራ ዘርፍ መሰረት መሰማራት ለሚፈልጉ የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች በማህበር ተደራጅተው ወደ ስራ ለመግባት የሚያስችል ስራ ማስኬጃ ወጪ ለእያንዳዱ ማህበር በፕሮጅክት ጽህፍት ቤቱ ወይም በማህበሩ ተጠንቶ በሚቀርበው ቢዝነስ ፕላን መሰረት ድጋፍ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ የገንዘቡ መጠን በቅድሚያ በቦርዱ ወይም በቢሮው እንዲፀድቅ የሚደረግ ሆኖ የስራ ማስኪጃው ከአጠቃላይ የፕሮጀክት ወጪው 10 በመቶ መብልጥ የለበትም፣

16.1.4. በማህበር ለሚደራጁ ተቋቋሚዎች የሚሆን የመስሪያ ቦታ በከተማው አስተዳደር ካቢኔ ሲወሰን እንዲሰጣቸው ይደረጋል፣

16.1.5. በማህበር ለተደራጁ እና በመረጡት የስራ ዘርፍ ለመሰማራት የሚያስችል ግብዓት በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ እንዲቀርብ የሚደረግ ሆኖ የሚቀርበው የማምረቻ መሳሪያና የቁሳቁስ ድጋፍ የዋጋውን 40% (አርባ በመቶ) በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚሸፈን ሲሆን ቀሪው 60 በመቶ በተዘዋዋሪ ብድር እስከ አራት ዓመት ተጠቃሚው እንደከፍል ይደረጋል፡፡ የብድር አመላለሱ ለአንድ ዓመት የሚቆይ የችሮታ ጊዜ እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

16.1.6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 16.1.3. እና 16.1.5 የፕሮጀክቱ አጠቃላይ ወጪ ለአንድ ማህበር እስከ 10,000,000.00 (አስር ሚሊዮን ብር) ድረስ ይሆናል፡፡

16.1.7. ሌሎች ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በሚሰጠው ልዩ ልዩ ድጋፎች አቅም በፈቀደ መሰረት ድጋፍና ክትትል እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡በተሰማሩበት ሥራ ዘርፍ ውጤታማ መሆን እንዲችሉ ተጠንቶ ለሚቀርብ ብድር ጥያቄ ከአዲስ ብደርና ቁጠባ ተቋም የብድር አገልግሎት እንዲመቻችላቸው ይደረጋል፡፡

## 17. ከፍተኛ ገቢ ላላቸዉ ተጠቃሚዎች

በምዝገባ፣ የልየታ እና የመረጃ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 001 /2009 መሰረት ከፍተኛ ገቢ ያላቸዉ ተብለዉ ለተለዩ ተጠቃሚዎች የሚሰጡ ድጋፎች፡-

### 17.1. በዘላቂነት ስለማቋቋም፤

17.1.1. በመረጠው የስራ መስክ ጋር ተዛማችነት ያለው ስልጠና እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

17.1.2. የስልጠናው ጊዜ እስኪጠናቀቅ ድረስ በየቀኑ የትራንስፖርት እና የምሳ አበል ብር 150.00 (አንድ መቶ ሃምሳ) እንዲከፈል ይደረጋል፣

17.1.3. በመረጡት ሥራ ዘርፍ መሰረት መሰማራት ለሚፈልጉ የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች በማህበር ተደራጅተው ወደ ስራ ለመግባት የሚያስችል ስራ ማስኬጃ ወጪ ለእያንዳዱ ማህበር በፕሮጅክት ጽህፍት ቤቱ ወይም በማህበሩ ተጠንቶ በሚቀርበው ቢዝነስ ፕላን መሰረት ድጋፍ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ የገንዘቡ መጠን በቅድሚያ በቦርዱ ወይም በቢሮው እንዲፀድቅ የሚደረግ ሆኖ የስራ ማስኪጃው ከአጠቃላይ የፕሮጀክት ወጪው 10 በመቶ መብልጥ የለበትም፣

17.1.4. በማህበር ለሚደራጁ ተቋቋሚዎች የሚሆን የመስሪያ ቦታ በከተማው አስተዳደር ካቢኔ ውሳኔ እንዲሰጣቸው ይደረጋል፣

17.1.5. በማህበር ለተደራጁ እና በመረጡት የስራ ዘርፍ ለመሰማራት የሚያስችል ግብዓት በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ እንዲቀርብ የሚደረግ ሆኖ የሚቀርበው የማምረቻ መሳሪያና የቁሳቁስ ድጋፍ የዋጋውን 30% (ሰላሳ በመቶ) በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚሸፈን ሲሆን ቀሪው 70 በመቶ በተዘዋዋሪ ብድር እስከ አራት ዓመት ተጠቃሚው እንደከፍል ይደረጋል፡፡ የብድር አመላለሱ ለአንድ ዓመት የሚቆይ የችሮታ ጊዜ እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

17.1.6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 17.1.3. እና 17.1.5 የፕሮጀክቱ አጠቃላይ ወጪ ለአንድ ማህበር እስከ 10,000,000.00 (ሁለት ሚሊዮን ብር) ድረስ ይሆናል፡፡

17.1.7. ማህበሩ ያለውን ሀብት በማቀናጀት አዋጭ በሆኑ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ለመሰማራት ጥያቄ ካቀረበ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ጉዳዮን አጣርቶ እና የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ እንዲያገኙ ለከተማው አስተዳደር ለውሳኔ ያቀርባል፣

17.1.8. ሌሎች ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በሚሰጠው ልዩ ልዩ ድጋፎች አቅም በፈቀደ መሰረት ድጋፍና ክትትል እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡በተሰማሩበት ሥራ ዘርፍ ውጤታማ መሆን እንዲችሉ ተጠንቶ ለሚቀርብ ብድር ጥያቄ በህጉ መሠረት የብደር አገልግሎት እንዲመቻችላቸው ድጋፍ ያደርጋል፡፡

17.1.9. ሌሎች ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በሚሰጠው ልዩ ልዩ ድጋፎች አቅም በፈቀደ መሰረት ድጋፍና ክትትል እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

## 18. ድጋፍ ስለሚደረግበት ሁኔታ፤

18.1.1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 13.1 እና 13.2 እንዲሁም በአንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 14.1. የሚሰጠው የገንዘብ ድጋፍ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ወራት ወይም እንደአግባብነቱ በማንኛውም ጊዜ በስማቸው በሚከፈተው ሂሳብ ገቢ ይደረጋል፣

18.1.2. ለልማት ተነሺ አርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክቶች የሚውል የተዘዋዋሪው ፈንድ እንዲቋቋም ይደረጋል፣ አፈጻጸሙ በቦርዱ ወይም በቢሮው በሚቀርብ ጥያቄ መሰረት በከንቲባው ይጸድቃል፣

18.1.3. በፕሮጀክት ጥናቱ መሰረት የሚያስፈልገው ማሽነሪ ወይም የመስሪያ ቁሳቁሶች ግዥና አቅርቦት  በአዲስ ካፒታል እቃ ፋይናስ ንግድ ስራ አክሲዮን ማህበር በኩል የሚፈጸም ይሆናል፡፡

# ክፍል አምስት
# ወደፊት በልማት ምክንያት ስለሚነሱ አርሶ አደሮች
# ስለሚሰጥ ድጋፍና አተገባበር፤

19.ወደ ፊት በልማት ምክንያት ከይዞታቸው እንዲነሱ ስለሚደረጉ አርሶ አደሮች ስለሚሰጥ ድጋፍ፣

19.1. ወደፊት በልማት ምክንያት ከይዞታቸው እንዲነሱ ስለሚደረጉ የልማት ተነሺ አርሶ አደር ስለ ልማቱ ዓላማ፣ በቀጣይ ስለሚሰፍሩበት ቦታ፣ ስለሚሰጥ ካሳ እና መቋቋሚያ ድጋፍ መረጃ በአግባቡ በቅደሚያ እንዲያውቁትና ተገቢው ግንዛቤ እንዲያገኙ ይደረጋል፣

19.2. በተቻለ መጠን የአርሶ አደሩ በልማት ምክንያት ከይዞታው እንዲነሳ ከመደረጉ በፊት አስቀድሞ ቢያንስ ከአንድ ዓመት በፊት ፕሮጀክት ጽ/ቤቱም ሆነ አርሶ አደሩ እንዲያውቀው መደረግ ይኖርበታል፣

19.3. በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ባለሙያዎችና ከሚመለከተው አካላት ጋር በመሆን የስነልቦና ዝግጅት ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፣

19.4. በከተማ ልማት ምክንያት ከይዞታቸው እንዲነሱ ከመደረጉ በፊት በህጉ መሠረት በተገቢው የካሳ ክፍያ ስሌት እና ምትክ ቦታ በወቅቱ እንዲያገኙ ይደረጋል፣

19.5. ከይዞታቸው በሚነሱበት ጊዜ ለማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ ችግር እንዳይጋለጡ ነፃ የህግና የምክር አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፣

19.6. በሚከፈላቸው የካሳ ክፍያ አጠቃቀም ዙሪያ በዘላቂነት መጠቀም የሚያስችላቸውን ፕሮጀክት በመቅረጽ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ስልት በመቀየስ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፣

19.7. በተቻለ መጠን ባህላዊ እሴቶቻቸው በተጠበቀ መልኩ እና መሠረተ ልማት በተሟላበት ስፍራ እንደሰፍሩ እና በአንድ አካባቢ የሚሰፍሩበት ሁኔታ እንዲመቻች ሊደረግ ይችላል፣

19.8. በሚሰጣቸው ምትክ ቦታ ላይ ህጉ በሚፈቅደው እና አቅምን ያገናዘበ የዲዛይን ስራ ተሰርቶ በቀላሉ ወደ ግንባታ እንዲገቡ ሁኔታዎች እንዲመቻቹ ይደረጋል፡፡

19.9. ከሚነሱበት ቦታ ጋር ተያይዞ የሚፈጠር የስራ እድል ካለ እና ከአርሶ አደር እና ከቦታው ፕሮጀክት ጋር ተመጣጣኝ እውቀት፣ ችሎታና ፍላጎት የሚኖር ከሆነ በስምምነት ቅድሚያ ተጠቃሚ እንዲሆን በፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ በኩል ሊመቻች ይችላል፣

19.10. ተደራጅተው ወደ ሥራ ለሚገቡት የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች በተዘጋጀ እና በመረጡት የቢዝነስ ፕላን መሰረት ወደ ኢንቨስትመንት እንዲሸጋገሩ የሚያስችል የብድር፣ የመሳሪያ ሊዝ እና ሌሎች የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ድጋፎች በህጉ መሰረት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ድጋፍ ይደረጋል፣

19.11. በልማት ምክንያት ከይዞታቸው እንዲነሱ የሚደረጉ አርሶ አደሮች የቦታው ማስተር ፕላን እና የአካባቢ ልማት ፕላን የሚፈቅድ እና አርሶ አደሩ በመሬት አጠቃቀም መሰረት የማልማት አቅም እና ፍላጎት ካለው በይዞታው ላይ ቅድሚያ የማልማት መብት እና ወደ ኢንቨስትመንት የሚገባበት እድል በአስተዳደሩ ይፈቀዳል፣

19.12. በማስፋፊያ ክልል ውስጥ ስላሉ አርሶ አደሮች ስለይዞታቸው አጠቃቀም በተመለከተ የአርሶ አደር የይዞታ መጠቀሚያ ሰርተፍኬት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

# ክፍል ስድስት

# የባለድርሻ አካላት ሚና

## 20. የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋም ፕሮጀክት ተጠቃሚዎች ሚና

20.1. ከአለበት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ችግር በፍጥነት ለመውጣት ሠርቶ መለወጥ የሚቻል መሆኑን አምኖ በመቀበል እና ባሉ የስራ አማራጭ መስኮች በመሰማራት ራስን ለመርዳት፣ ከሌሎች ጋር ለመስራትና ሀገርን ለማልማት ዝግጁ መሆን ይኖርበታል፣

20.2. የሚሰጡትን ድጋፎች በአግባቡ በመጠቀም እድገት ለማስመዝገብ ዝግጁ መሆን፣

20.3. ምርትን በጥራት፣ በወቅቱ እና በተሻለ ዋጋ በማቅረብ ተወዳዳሪ መሆን ይኖርበታል፣

20.4. ከጠባቂነት ስሜት በመላቀቅ፣ የውስጥ ችግሮችን በራስ አቅም በመፍታት፣ ራስን በክህሎትና በቴክኒክ በማብቃት ዉጤት ለማምጣት ዝግጁ መሆን፣

20.5. የቁጠባ ባህሉን ማዳበርና የተሰጠውን የኑሮ ማሻሻያ ብድር በአግባቡ መመለስ ይኖርበታል፣

20.6. ትክክለኛ መረጃዎችን የመስጠት፣ ሐሰተኛ መረጃዎችና የተሳሳቱ ተግባራትን ያለመፈጸም እና መፈጸማቸዉን ሲያወቅ ወዲያዉኑ ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## 21. የህብረተሰቡ ሚና

21.1. ግልፀኝነትና ተጠያቂነት ያለዉ አሰራር እንዲሰፍን የድርሻውን ይወጣል፣

21.2. ፕሮጀክቱ በታለመለት ዓላማ መሠረት ተፈጻሚ እንዲሆን ከአስተዳደሩ እና ከአርሶ አደሩ ጋር ተባብሮ እና ተቀናጅቶ ይሰራል፣

21.3. ትክክለኛ መረጃዎችን በመስጠትና ሀሰተኛ መረጃዎችን በማጋለጥ ተሳትፎ ያደርጋል፡፡

## 22. የአስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ሚና

### 22.1. የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ ሚና፤

22.1.1. የልማት ተነሺ ስለሆኑ እና ወደፊትም ሊነሱ ስለሚችሉ አርሶ አደሮች ዝርዝር መረጃና ስለ ተሰጣቸው የካሣ ክፍያ ሙሉ መረጃ መስጠት አለበት ፣

22.1.2. አርሶ አደሮችን በማቋቋም ረገድ የመሬት አቅርቦትን ለሚጠይቅ ሥራ እና ፕሮጀክት መሰረት መሬት አዘጋጅቶ ለካቢኔው ያቀርባል፤ በውሳኔው መሠረት ያስፈጽማል፣

22.1.3. በከተማው ክልል ውስጥ ላሉ አርሶ አደሮች የይዞታ የመጠቀሚያ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ይሰጣል፣

22.1.4. ለልማት ተነሺ አርሶ አደሮች በህጉ መሰረት የለማ ምትክ መሬት ያቀርባል፣

22.1.5. አርሶ አደሩን የተመለከቱ የካሳ ክፍያ እና ሌሎች ተዛማጅ መብቶች ጋር የሚያያዙ ጥናቶች እና ውሳኔዎች ላይ ፕሮጅከት ጽህፈት ቤቱ እንዲሳተፍ ያደርጋል፣

22.1.6. የልማት ተነሺ አርሶ አደሮችን ከማቋቋም አንጻር ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አስፈላጊዉን ድጋፍና ትብብር ያደርጋል፣

22.1.7. ሌሎች ከቢሮው ወይም ከፕሮጀክት ጽህፈት ቤት የሚጠበቁ ድጋፎችን ያደርጋል፡፡

### 22.2. የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሚና

22.2.1. ለስትራቴጂው ማስፈፀሚያ በጀት ይመድባል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣

22.2.2. የተቀረጹ ፕሮጀክቶችን እንዳአስፈላጊነቱ ይገመግማል፣ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣

22.2.3. ተጠቃሚዎችን በማቋቋም ረገድ እንደ አሰፈላጊነቱ በቅንጅት ይሰራል፣

22.2.4. የተዘዋሪ ፈንድ እንዲደራጅና እንዲጠናከር ያደርጋል፣

22.2.5. ሌሎች ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚጠበቁ ድጋፎችን ይሰጣል፡፡

### 22.3. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ሚና

22.3.1. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በለያቸው የስራ ዘርፎች ላይ የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣

22.3.2. ተጠቃሚዎችን ከማደራጀት አንጻር የአደረጃጀት ድጋፍ ያደርጋል፣

22.3.3. የስራ ዕድል ፈጠራ ልየታና የገበያ ትስስርን ያመቻቻል፣

22.3.4. እንደአስፋላጊነቱ ተቋቋሚዎቹ የመስሪያ ቦታ እንዲያገኙ ያደርጋል፣

22.3.5. ለተጠቃሚዎች ከሌሎች ኢንተርፕራይዞች ጋር የልምድ የክህሎት የእዉቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚያደረጉበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣

22.3.6. በሚዘጋጁ ባዛሮች ኢግዝቢሽኖች ምርታቸዉን እንዲያስተዋዉቁ ያመቻቻል

22.3.7. ተጨማሪ አዋጭ የስራ ዘርፎች ይለያል፣

22.3.8. በተለየው አዋጭ የስራ ዘርፍ እና ዕድገት ተኮር ስራዎች እንዲሸጋገሩና እንዲሰማሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣

22.3.9. ሌሎች ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚጠበቁ ድጋፎችን ይሰጣል፡፡

## 22.4. የንግድ ቢሮ ሚና

22.4.1. ተደራጅተው መስራት የሚፈልጉ አርሶ አደሮችን በማህበር ያደራጃል፣ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣

22.4.2. በየሥራ ዘርፎቹ ስራዎችን በመለየት አርሶ አደሮች ተጠቃሚ እንዲሆኑ እገዛ ያደርጋል፣

22.4.3. በጥናት ላይ በተመሰረተ መረጃ በየሥራ ዘርፎች እምቅ ሀብት እንዲስፋፉ የሚያስችል ምርምርና ጥናት ያካሂዳል፣

22.4.4. በሚቀርብለት የድጋፍ ጥያቄ መሰረት በየሥራ ዘርፎች መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማጠናከርና በመተንተን ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ያቀርባል፣

22.4.5. በሚመቻች የሥልጠና መድረክ ስለንግድ፣ስለንግድ ህግ እና ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ ያስጨብጣል፣

22.4.6. ለተጠቃሚዎች አስፈላጊ ግብዓቶችን እና ቴክኖሎጂዎችን ከበቂ ስልጠና ጋር ያቀርባል፣

22.4.7. የገበያ ጥናት በማድረግ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፡፡

22.4.8. ሌሎች ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚጠበቁ ድጋፎችን ይሰጣል፡፡

## 22.5. የጤና ቢሮ ሚና

22.5.1. የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች በሰፈሩበት አካባቢዎች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መሠረታዊ የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ የጤና ተቋማት ይገነባል፣

22.5.2. ግንባታቸው የተጠናቀቀ የጤና ተቋማት የህክምና ባለሙያዎች የህክምና መሣሪያዎችና መድሐኒቶች በማሟላት አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋል፣

22.5.3. የበሽታ መከላከልና ህክምና አገልግሎት ሥልጠና ይሰጣል ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣

22.5.4. ሌሎች ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚጠበቁ ድጋፎችን መስጠት፡፡

## 22.6. የትምህርት ቢሮ ሚና

22.6.1. የልማት ተነሺ የሆኑ አርሶ አደሮች በአቅራቢያቸው ት/ቤቶች እንዲገነቡ ያደርጋል፣

22.6.2. ለትምህርት ቤቶቹ አስፈላጊውን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችና መምህራን በማሟላት የማስተማር አገልግሎት እንዲጀምሩ ያደርጋል፣

22.6.3. የልማት ተነሽ የሆኑ የአርሶ አደር ልጆች ትምህርታቸው እንዳይስተጓጎል ያደርጋል፣

22.6.4. ማንበብና መጻፍ የማይችሉ አርሶ አደሮች መሠረታዊ ትምህርት የሚያገኙበትን ሁኔታ መንደፍ ተግባራዊ ያርጋል፣

22.6.5. ሌሎች ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚጠበቁ ድጋፎችን ይሰጣል፡፡

## 22.7. የመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ሚና

22.7.1. የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች በሚኖሩበት አካባቢ የመንገድ መሠረተ ልማት እንዲሟላ ያደርጋል፣

22.7.2. ተጠቃሚዋች ስለ መንገድ አጠቃቀም በቂ እዉቀት እንዲኖራቸዉ ያደርጋል፣

22.7.3. በዚህ መመሪያ ድጋፍ እንዲደረግላቸው ለተወሰነላቸው ተጠቃሚዎች ነፃ የመንግስት የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፣

22.7.4. ለተዘረጉት መንገዶች ወቅታዊ የጥገና አገልግሎት እንዲደረግላቸው ያደርጋል፣

22.7.5. ሌሎች ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚጠበቁ ድጋፎችን መስጠት፡፡

## 22.8. የኮንስትራክሽን ቢሮ ሚና

22.8.1. ከአካባቢ ፕላን ጋር የተጣጣመ እና ባህላዊ እሴቶችን መሠረት ያደረገ ዲዛይን በማዘጋጀት ድጋፍ ያደርጋል፣

22.8.2. በዚህ መመሪያ የመስሪያ እና መጠለያ ግንባታ እንዲገነባ ለተፈቀደላቸው ተቋቋሚዎች የዲዛይን ፣ ግንባታ እና ተያያዥነት ያላቸውን ድጋፎች ያደርጋል፣

22.8.3. ለተጠቃሚዎች አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ግንባታዎችን ማከናወን የግንባታ ሂደቱን መከታተል በወቅቱ አስፈላጊ እርማት እንዲወሰድ ያደርጋል፣

22.8.4. ሌሎች ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚጠበቁ ድጋፎችን መስጠት፡፡

## 22.9. የኢንዱስትሪ ቢሮ

22.9.1. አዋጭ የኢንቨስትመንት እና የኢንዱስትሪ ዘርፍ የስራ መስኮችን በመለየት ለተቋቋሚዎቹ መረጃ ያቀርባል፣

22.9.2. በአነስተኛና መካከለኛ ማንኒፋክቸሪንግ ላይ የሚሰማሩ ተቋቋሚዎች የስራ ላይ ልምምድ በማድረግ የልምድ ልውውጥ እንዲቀስሙ፣ መልካም ተሞክሮዎችም ተቀምረው እንዲስፋፉ ያደርጋል፣

22.9.3. እንደአስፋላጊነቱ ተቋቋሚዎቹ የመስሪያ ቦታ እንዲያገኙ ያደርጋል፣

22.9.4. እንዳስፈላጊነቱ የግንዛቤ ማስጨበጥ ትምህርትና ስልጠና እንዲሁም የቴክኒክ ድጋፎችን ያደርጋል፣

22.9.5. ሌሎች ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚጠበቁ ድጋፎችን መስጠት፡፡

## 22.10. የአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም ሚና

22.10.1. የብድር አገልግሎት ያመቻቻል፣

22.10.2. በቁጠባ ባህል መዳበር ላይ የሙያ ምክር ይሰጣል፣

22.10.3. የቁጠባና ብድር እንቅስቃሴቸዉን ይከታተላል እንዲሁም አስፈለጊ ድጋፎችን ያደርጋል፣

22.10.4. ተገቢ የፋይናስ እንቅስቃሴ መረጃዎችን በማሰባሰብ እና በማደራጀት ይይዛል እንዲሁም ጥቅም ላይ እንዲዉሉ ያደርጋል፣

22.10.5. ሌሎች ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚጠበቁ ድጋፎችን ይሰጣል፡፡

## 22.11. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ ሚና

22.11.1. የክህሎት ስልጠና እና የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ያከናውናል፣

22.11.2. መልሶ ተቋቋሚዎች በመረጡት የስራ መስክ ላይ የክህሎት ስልጠና ይሰጣል፣

22.11.3. ባገኙት የሙያ ክህሎት መሰረት ውጤታማ መሆናቸውን ይከታተላል ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋል፣

22.11.4. ከተለያዩ ተቋማት ጋር በዘርፉ የሙያ ልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ያመቻቻል፣

22.11.5. በተሰጡ ስልጠናዎች ላይ የፋይዳ ግምገማ እንዲካሄድ ያደርጋል፣

22.11.6. ሌሎች ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚጠበቁ ድጋፎችን ይሰጣል፡፡

## 22.12. የአዲስ ካፒታል እቃ ፋይናስ ንግድ ስራ አክሲዮን ማህበር፣

22.12.1. የካፒታል ዕቃዎች ግዥ ናሙና ጥናት ከፕሮጀክቶች አኳያ ቅድመ ጥናት ያቀርባል፣

22.12.2. የግብዓት አቅርቦት ግዥ ላይ የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣

22.12.3. ለፕሮጀክቱ አስፈላጊ የሆኑ የአቅርቦት ግዥ እና የፋይናንስ ድጋፍ ያመቻቻል፣

22.12.4. የመሳሪያ መግዣ ብድር ወይም የመሳሪያ ሊዝ አቅርቦት አገልግሎት ይሰጣል፣

22.12.5. ለሚያቀርባቸዉ መሳሪያዎች አስፈላጊ የሆኑ ድጋፎችን ያደርጋል

22.12.6. ሌሎች ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚጠበቁ ድጋፎችን ይሰጣል፡፡

## 22.13. የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከል ሚና

22.13.1. በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ በኩል የክህሎትና የሙያ ስልጠና ያገኙ ተቋቋሚዎችን ብቃት ይመዝናል፣

22.13.2. ምዘናውን በአግባቡ ላከናወኑ እና ብቁ ለሆኑ ተቋቋሚ ሰልጣኞች የምዘና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣

22.13.3. ሌሎች ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚጠበቁ ድጋፎችን ይሰጣል፡፡

## 22.14. የውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ሚና

22.14.1. የልማት ተነሺ የሆኑ አርሶ አደሮች በሚኖሩበት ቦታና በሚሰሩበት አካባቢ የውሃ መሠረተ ልማት ዝርጋታ እንዲከናወን ያደርጋል፣

22.14.2. የውሃ እና የፍሳሽ ማንሳት አገልግሎቶች እንዲያገኙ ያደርጋል፣

22.14.3. በክፍያ እና በሌሎች አገልግሎቶች አፈጻጸም ሂደት ቀልጣፋ እንዲሆን ተገቢዉን ድጋፍ ያደርጋል፣

22.14.4. ሌሎች ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚጠበቁ ድጋፎችን ይሰጣል፡፡

## 22.15. የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን

22.15.1. ከአካባቢ ጋር ተስመሚ የሆኑ የሥራ ዘርፎችን በመለየት ለተጠቃሚዎች ቅድሚያ በመስጠት እንዲሰማሩባቸዉ ያደርጋል፣

22.15.2. በሚሰማሩበት የስራ ዘርፍ ከአካባቢ ደህንነት ጋር ሰለሚኖረዉ መስተጋብርና ጥናት ያደርጋል፣

22.15.3. የካባ ምርት ቦታዎችን በመለየት ለተጠቃሚዎች መረጃ ያሰራጫል፣ የካባ ምርት ስራ ላይ መሰማራት የሚፈልጉ ካሉ የስራ ቦታ እና የመጠቀሚያ ፈቃድ እንዲያገኙ ያደርጋል፣

22.15.4. አዋጭ እና ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆኑ የዕጽዋት ዝርያዎችን ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

22.15.5. ሌሎች ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚጠበቁ ድጋፎችን ይሰጣል፡፡

## 22.16. የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል እና አገልግሎት ሚና

22.16.1. የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች በሚሰሩበት አካባቢ የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት እንዲሟላ ያደርጋል፣

22.16.2. የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች የሚኖሩበት አካባቢ የኤሌክትሪክ አልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፣

22.16.3. በክፍያ እና በሌሎች አገልግሎቶች አፈጻጸም ሂደት ቀልጣፋ እንዲሆን ተገቢዉን ድጋፍ ያደርጋል፣

22.16.4. ሌሎች ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚጠበቁ ድጋፎችን ይሰጣል፡፡

## 22.17. የኢፌዲሪ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ሚና

22.17.1. የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት የሚከናወንባቸውን አካባቢዎችና በልማቱ ምክንያት የተነሱ ወደፊትም ሊነሱ የሚችሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች ዝርዝር መረጃ ይሰጣል፣

22.17.2. የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች ለማቋቋም ኮርፖሬሽኑ የነደፈውን ዕቅድና የያዘውን በጀት በተመለከተ መረጃ ይሰጣል፣

22.17.3. በሚገነቡ ኢንዱስትሪዎች የልማት ተነሺ የሆኑ አርሶ አደሮች አብቅቶ የቅጥር ዕድል የሚያኙበትን ሁኔታ እንዲመቻች ያደርጋል፣

22.17.4. የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች የማቋቋም ተግባር ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ጋር ተቀናጅቶ ይሰራል፣

22.17.5. በሚገነቡ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የምርት መሸጪያ እና ሌሎች አገልግሎት መስጫ ሼዶችን በልማት መክንያት ተነሺ ለሆኑ እና ለሚሆኑ አርሶ አደሮች ቅድሚያ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

22.17.6. ሌሎች ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚጠበቁ ድጋፎችን ይሰጣል፡፡

## 22.18. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሚና

22.18.1. ከመልሶ ማልማት እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ በጋራ ጥናት ያካሂዳል፣

22.18.2. የየአዋጪነት ጥናት እና የፋይዳ ግምገማ (impact assessment) እንዲካሄድ በትብብር ይሰራል፣

22.18.3. ከከተማው አርሶአደሮች ጋር ተያያዙ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ባህላዊ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ጋር ጥናትና ምርምር ለማካሄድ በቅንጅትና በትብብር ይሰራል፣

22.18.4. ሌሎች ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚጠበቁ ድጋፎች ላይ ትብብር ያደርጋል፡፡

## 22.19. የማህበራዊ ጥበቃ ፈንድ እና ልማታዊ ሴፍቲኔት ኤጀንሲ

22.19.1. በተጠቃሚ ልየታ መስፈርት መሠረት የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ለሚያስፈልጋቸዉ ቅድሚያ በመስጠት ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

22.19.2. አቅመ ደካሞችንና አካል ጉዳተኞች እንዲሁም እድሜያቸው ለስራ ያልደረሱትንና በትምህርት ገበታ ላይ የሚገኙትን የልማት ተነሽ አርሶ አደር ቤተሰቦች ቅድሚያ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

22.19.3. እንደአስፈላጊነቱ በቢሮው ወይም በቦርድ እየተወሰነ ከማህበራዊ ጥበቃ ፈንድ የሀብት ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፣

22.19.4. ከልማት ተነሽ አርሶ አደሮች ፕሮጀክት ጸ/ቤት ጋር በትብብር ይሰራል፡፡

# ክፍል ስድስት

# ክልከላ ፤ኃላፊነት እና ቅሬታና አቤቱታ የማቅረብ መብት

## 23. የተከለከሉ ድርጊቶች፤

23.1. በልማት ምክንያት ተነሺ የሆነ አርሶ አደር ቤተሰቡ ያልሆኑትን ቤተሰቦቼ ናቸዉ ብሎ ለድጋፍ ማስመዝገብና ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ ፣

23.2. ትክክለኛ የራሱንና የቤተሰቡን ገቢና እና የገቢ ምንጭ ወይም ሀብት ያልሆነዉን ማስመዝገብ፤

23.3. በተለየው የፕሮጀክት የስራ መስክ ከአንድ የስራ መስክ ውጭ በተለያዩ የስራ መስኮች ላይ ለመሳተፍ መሞከር እና ተሳትፎ መገኘት፣

23.4. በልማት ተነሺ አርሶ አደሩም ሆነ በቤተሰቡ ከአንድ ጊዜ በላይ ከሚመለከተዉ የመመዝገቢያ ቦታ ዉጪ በተለያዩ የምዝገባ ቦታዎች ለፕሮጀክት ጽ.ቤቱ ሳያሳዉቁ፣ ሳይፈቃድላቸዉ ያለበቂ ምክንያት ድጋፍ ለማግኘት ተመመዝገቦ መገኘት ፣

23.5. ከአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ውጪ የሆነ እና በልማት መክንያት ተነሺ አርሶ አደር ያልሆነ እንዲሁም በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን መስፈርት ሳያሟሉ ድጋፍ ለማግኘት መሞከር፤

23.6. ከዚህ የድጋፍ አጠቃቀም መመሪያ ጋር አባሪ ሆነው ከቀረቡት የምዝገባና የፍላጎት ማሳወቂያ ቅጾች ውጪ በሌላ ቅፅ ወይም ፎርም መረጃን ሞልቶ ማቅረብ፤

23.7. የፕሮጀክት ጽ/ቤቱን መመሪያዎች እና አሰራሮች በተዛባ መልኩ መግለጽ እና ሥራ ላይ ማዋል፤

23.8. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለሚጠይቃቸዉ መረጃዎች ህጋዊ ድጋፎች በወቅቱ ያለመሥጠትና ተገቢዉን ትብብር ያለማድረግ ክልክል ነው፡፡

## 24. የድጋፍ ፈላጊው ኃላፊነት

24.1. ተጠቃሚው ድጋፍ ለማግኘት በቅድሚያ በዚህ መመሪያ የተቀመጠውን መስፈርት አሟልቶ በግንባር ወይም በህጋዊ ወኪሉ አማካኝነት መቅረብና ትክክለኛ መረጃ መስጠት ይኖርበታል ፡፡

24.2. ማንኛውም በዚህ ፕሮጀክት ተጠቃሚ ለመሆን መስፈረት የሚያሟላ ሰው በምዝገባ፣ የልየታ እና የመረጃ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 001 /2009 መሰረት የተመዘገበ እና የድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻ በመያዝ በአካል ወይም በዉልና ሰነዶች ማረጋገጫ ጽ/ቤት ህጋዊ ዉክልና በተሰጠዉ ወኪሉ አማካኝነት በመቅረብ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በሚያሳዉቀዉ የምዝገባ ማስታወቂያ መሰረት በተዘጋጀዉ ህጋዊ የመመዝገቢያ ቅጽ እና የምዝገባ ፈጻሚ ባለሙያ የመመዝገብ፤

24.3. ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚሠጡትን ማስረጃዎች በአግባቡ የመያዝና በተጠየቀም ጊዜ የማቅረብ፤

24.4. በተጠቃሚነቱ የሚሰጡትን ድጋፎች በአግባቡ የመጠቀም ለሌላ ላልተፈቀደለት አካል አሳልፎ ያለመስጠት፤

24.5. ማንኛውም የድጋፍ ማዕቀፍ ተጠቃሚ በድጋፍ አሰጣጥ ሂደት ሕገ-ወጥ ድርጊቶችና ከመመሪያው ውጭ እየተፈጸሙ ያሉ ተግባራቶች ካጋጠሙት ጉዳዩን ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ወይም ለሚመለከተው አካል የመጠቆም እና የማስረዳት፤

24.6. በዚህ ፕሮጀክት ተጠቃሚ እንዲሆን የተለየ አካል ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በወሰናቸው የምዝገባ ቦታዎች በአካል ወይም በህጋዊ ወኪሉ በመቅረብ በመመሪያው በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የድጋፍ ጥያቄ ማቅረብ ግዴታ አለበት፤

## 25. የድጋፍ አመቻችና የመዝጋቢው አካል ኃላፊነት

25.1. ድጋፍ አመቻቹ ስለ አመዘጋገብ ሂደት፣ ስለፕሮጀክቶቹ ዐይነት፣ ስለ አማራጭ የስራ መስኮች እንዲሁም ስለ ድጋፍ አሰጣጥ ስርዓት በቅድሚያ ለድጋፍ ጠያቂው በቂ መረጃ መስጠት አለበት፣

25.2. ስለቅጾች አሞላል፣ ስለማመልከቻ አቀራረብ፣ ስለኃላፊነት፣ ስለተጠያቂነት እና ስለ መልሶ ማቋቋም ዓላማ በቂ መረጃ ለተጠቃሚዎች ገለጻና ድጋፍ የመስጠት፣

25.3. ለድጋፍ አገልግሎት በምዝገባና ልየታ መመሪያ የተለየው  በተመዝጋቢው የተሞሉት ቅፆች በባህር መዝገብ እና በመረጃ ቋቱ ውሰጥ ከመግባታቸው በፊት በአግባቡ  ማጣራት ይኖርበታል፣

25.4. በልየታ መመሪያ እና በድጋፍ መመሪያዎች ለድጋፍ አገልግሎት ተለይቶ ባቀረበው ጥያቄ መሰረት ድጋፍ ሲመቻች በተጠቃሚው በሚሞላ መነሻ ቅጽ ፋይል እንዲከፈት ያደርጋል፤

25.5. ቅሬታ ለሚያቀርቡ ተገልጋዮች አፈጣኝ የሆነ ምላሽ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፣

25.6. ተመዝጋቢዎች ስለመመዝገባቸው እና ስለታቀፉበት ድጋፍ ማዕቀፍ የሚያስረዳ ወይም የሚያረጋግጥ ማስረጃ ደረጃውን የጠበቀ የምዝገባ ማስረጃ መታወቂያ ወይም ሰርተፊኬት መስጠት ይኖርበታል፣

25.7. የተመዝጋቢዎችን የድጋፍ አገልግሎት አሰጣጥ መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡

### 26.የቅሬታና አቤቱታ የማቅረብ መብት

ማንኛውም የድጋፍ ማዕቀፍ መመሪያ ተጠቃሚ ከሂደቱ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ቅሬታዎችን በቅድሚያ ለየቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የቅሬታ ሰሚ አካል  በወቅቱ የማቅረብ መብት አለው፡፡ ቅሬታው ካልተፈታለት ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ እና በየደረጃዉ ላለ አካል ማቅረብ ይችላል::

## 27. ስለ ቅሬታና አቤቱታ አቀራረብ

በመልሶ ማቋቋሚያ ድጋፍ ማዕቀፍ እና ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ የሚቀርብ ቅሬታና አቤቱታ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የቅሬታ አቤቱታ አቀራረብና አፈታት መመሪያ መሠረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

# ክፍል ሰባት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 28. ልዩ ልዩ ድጋፎች ስለሚደረጉበት አግባብ

28.1. በሚመለከታቸው ተቋማት የጤና፣ የትምህርት፣ የባህል፣ የትራንስፖርት እና ሌሎች መሰረተ ልማቶች በዕቅድ ተይዘው እንዲሟሉ ይደረጋል፡፡

28.2. በዚህ መመሪያ እንዲሰጡ ከተሰጡት ድጋፎች በተጨማሪ ሌሎች ልዩ ልዩ ድጋፎች ሲገኙ በፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ አቅራቢነት በቢሮው ወይም በቦርድ እየተወሰነ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

## 29.የመተባበር ግዴታ፤

ማንኛውም ሰው ይህን መመሪያ ከማስፈጸም አኳያ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## 30.ቅጣት፤

30.1. ማንኛውም ተመዝጋቢ በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩትን አንቀፆች በመተላለፍ የተመዘገበ፣ለመመዝገብ የሞከረ፣ያሳሳተ፣የምዝገባውን ሂደት ያወከ፣ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት የሞከረ፣ ሀሰተኛ ሰነድ ያቀረበ እንደሆነ እና የዚህን መመሪያ ድንጋጌ የተላለፈ በሀገሪቱ የወንጀል ህግ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች መሠረት ተጠያቂ እንዲሆን ስልጣን ላለው አካል በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በኩል ክስ እንዲቀርብበት ይደረጋል፣

30.2. በዚህ መመሪያ የተጣለውን ግዴታ ያልተወጣና ክልከላዎችን የጣሰ ማንኛውም አስፈጻሚና ፈጻሚ ሰራተኛ ወይም የስራ ኃላፊ ከሆነ በሀገሪቱ የወንጀለኛ ህግ ድንጋጌዎች ተጠያቂነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንግስት ሠራተኞ አዋጅ እና በአቤቱታ የቅሬታ እና አቤቱታ አቀራረብ ፣ ምርመራ፣ አወሳሰንና ተጠያቂነት ደንብ ቁጥር 78/2008 መሠረት በዲሲፕሊን ቅጣት እንዲከሰስ ይደረጋል፣

## 31.ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 32. መመሪያ የማሻሻል ስልጣን

ይህን መመሪያ ማሻሻል ሲያስፈልግ ቢሮው ሊሻሻል ይችላል፡

### 33. የትርጉም አሻሚነትን በተመለከተ

በዚህ መመሪያ የተገለጹ ቃላቶች እና ዐርፍተ ነገሮች አሻሚ ትርጉም የሚሰጡ ሆነዉ በተገኙ ጊዜ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚሰጠዉ ተርጉም የመጨረሻ ትርጉም ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

### 34. መመሪያዉ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሀምሌ ወር 2009ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ**

**2009 /አዲስ አበባ**

<u>የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋ ም ፕሮጀክት ጽ/ቤት</u>

በድጋፍ ማዕቀፍ መመሪያ መሠረት የተገልጋይ ጥያቄ ማቅረቢያ ቅፅ-7

1.የአገልግሎት ፈላጊ አጠቃላይ መረጃ

- የአመልች ሙሉ ስም_________________ ፃታ___ዕድሜ_________ ት/ደረጃ______________
- የበላቤት ሙሉ ስም__________________ ፃታ___ ዕድሜ________ ት/ደረጃ______________
- የመኖሪያ አድራሻ፡-ክ/ከተማ____________ ወረዳ_________ ልዩ ቦታ_____________
  ቤት ቁጥር____________ ስልክ ቁጥር_________________
- የቤተሠብ አባለት ብዛት፡- ወ___________ ሴ____________ ድ___________
- ከ5ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት፡-ወ_______ ሴ____________ ድ___________
- ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸዉ፡- ወ______________ ሴ___________ ድ___________

2.የሚፈለግ አገልግሎት ዓይናት

- የቀጥታ ድጋፍ
- ምንም ገቢ የሌላቸው ድጋፍ
- ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው
- መካከለኛ ገቢ ያላቸው
- ከፍተኛ ገቢ ያላቸው

3.መሟለት የሚገባቸዉ ቅድመ ሁኔታዎች በአገልግሎት ጥያቄ ተቀባይ ባለሙያ የሚሞለ፡-

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

4.ለአገልግሎት ጠያቂዉ የተሠጠ መረጃ እና ቀጣይ ቀጠሮ፡- ________________________________

______________________________________________________________________________

_______

5.የአገልግሎት ጥያቄ የተመረለት ሥራ ክፈል/ባለሙያ፡-____________________________________

______________________________________________________________________________

6.የአገልግሎት ጠያቂ

ሥም_______________________

ፊርማ_______________

ቀን__________